# ጾም

ጾም ማለት ሰውነት ከሚፈልጋቸው ነገሮች ሁሉ መከልከል ወይም ለሰውነት የሚያምረውን የሚያስጐመኘውን ነገር መተው ማለት ነው። ሃይማኖት ባለበት ቦታ ሁሉ ጾም አለ። ጾም ከሃይማኖት ጋር ዘለዓለማዊ ዝምድና አለው። ይልቁንም በብሉይ ኪዳን ጾም ከፍተኛ ቦታ አለው። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ከእግዚአብሔር ጋር በሚገናኙበት ወራት እህል ውኃ ባፋቸው አይገባም ነበር። ዘጸ 34:28። በኃጢአት ብዛት የታዘዘው የእግዚአብሔር መዓት የሚመለሰው ቁጣው የሚበርደው ሕዝቡ በጾም ሲለምኑትና ሲማልዱት ነበር። ዮናስ 3:5-10።

በአዲስ ኪዳንም ጾም ሰው ሠራሽ ሕግ ሳይሆን ራሱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው የሥራ መጀመሪያ አድርጐ የሠራው ሕግ ነው። ማቴ 4:2፣ ሉቃ 4:2። መድኃኒታችን በስስት፣ በፍቅረ ንዋይና በትዕቢት የሚመጣብንን ጠላት ዲያብሎስ በጾም ድል እንደምናደርገው አሳየን። አርአያ ሆነን። ይህም ብቻ ሳይሆን በቁራኝነት አብሮ የሚኖር ርኩስ ሰይጣን እንኳን በጾም የሚወገድ መሆኑን መድኃኒታችን ተናግሯል። ማቴ 17:21፣ ማር 9:2። በዚሁ መሠረት በጾም ከሰይጣን ቁራኝነት መላቀቅ ለእኛ ታላቅ ጸጋ እና ኃይላችን ነው።

ቤተክርስቲያንን እንዲያገለግሉ የታዘዙ ሐዋርያትም ከመንፈስ ቅዱስ በየጊዜው ትእዛዝ የሚቀበሉት በጾምና በጸሎት ላይ እያሉ ነበር። የሐዋ 13:2። ይህም የሚያመለክተው ጾምና ጸሎት የማይነጣጠሉ መሆናቸውንና ስንጾም ስንጸልይ መንፈስ ቅዱስ እንደሚቀርበን ነው። በጾም የተዋረደ እና ለጸሎት የተጋ ሰውነት ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ የተዘጋጀ በመሆኑ እግዚአብሔር ያዝዘናል እኛም እንታዘዛለን። ለስብከተ ወንጌል የሚያገለግሉ ዲያቆናትና ቀሳውስት የሚሾሙትም በጾምና በጸሎት ነበረ። የሐዋ 13:3፣ 4:25። እነ ቆርኔሌዎስ ያላሰቡትን ክብር ያገኙት በጾምና በጸሎት ፈጣሪያቸውን ማልደው ነው። የሐዋ 10:20። ጾም እንኳን የጠበቅነውንና ያሰብነውን ቀርቶ ያላሰብነውንና ያልጠበቅነውን ፈጽሞም የማይገባንን ጸጋና ክብር የሚያሰጥ ነው።

የጾም ሃይማኖታዊ ትርጉም ፈጣሪን መለመኛ ከኃጢአት ቁራኛ መላቀቂያ መሣሪያ ስለሆነ በጾም ወራት ለአምሮት ለቅንጦት የሚበሉ ወይም ለመንፈሳዊ ኃይል ተቃራኒ የሆኑ ሥጋዊ ፍትወትን የሚያበረቱ የአልኮል መጠጦችን፣ ሥጋንና ቅቤን፣ ወተትና እንቁላልን ማራቅ ታዟል። ባልና ሚስትም በአንድ ምንጣፍ አይተኙም። 1ቆሮ6:5። «ነዳያንን ለመመገብ የሚጾም ንዑድ ክቡር ነው» እንደተባለ ጠመኛው ለምሳው ወይም ለእራቱ ያለውን ወጭ ነዳያንን እንዲረዳበት ለድኩማን ድርጅት ቢሰጥ ወይም በቤተክርስቲያን አካባቢ ለሚገኙ ነዳያን ቢመጸውት ጠሙን የበለጠ ክርስቲያናዊ ያደርገዋል።

ጾም የታሪክ ድርጊቶችን እያስታወሱ ከኃጢአት ለመንጻት ስለራስ የታሰበውን ለነዳያን በመስጠት የሚጾም መሆኑን መረዳት አለብን። ጾም ለራስ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ለወዳጅ ብቻ ሳይሆን ለጠላትም ይጾማል። በዲድስቅልያ 1:5 «ለሚያሳድዱህ ጹምላቸው» ተብሏል። በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ የተያዙትን በስደትና በምርኮ ያሉትንም በጾም ወራት ማስታወስና ስለእነርሱ መጸለይ ይገባል። ቅዱስ ያሬድ ክፉ ከማየት ክፉ ከመናገር እና ክፉ ከመስማት ጭምር መጾም እንደሚገባ ተናግሯል።

በቅዱሳን ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ባሕልና ትውፊት መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከመጀመሪያዎቹ አብያተ ክርስቲያናት አንዷ ስለሆነች የጾም ሕግና ሥርዓት አላት። እነዚህም ሰባት የጾም ወራት ናቸው። ከእነዚህም ዓበይት አጽዋማት ዐቢይ ጾምን እንመለከታለን።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ጾም የጾመው ለአብነት፣ ለማስተማር፣ ለአርዓያ ነው። በዚህ ታላቅ ጾም ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ፣ ከሰው የሥጋ ጠባይ የሚመጣ ስስትና ፍቅረ ንዋይ ድል የተነሱበት ነው። እኛም ይህን እያሰብን በተለያየ መንገድ የሚመጣብንን ፈተና ለማራቅ ከዚህ ታላቅ ጾም በረከት እንድናገኝ እንጾማለን። ጸልዮ ጸልዩ፣ ጾሞ ጹሙ ብሎናል። ማቴ. 6፣16። ስለዚህም ትእዛዙን ለማክበር እንጾማለን።

የዚህ ታላቅ ጾም ስያሜዎች፡-

1. ዐቢይ ጾም

የባሕርይ አምላክ በሆነዉ በጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተመሠረተ በመሆኑ ዐቢይ ወይም ታላቅ ጾም ይባላል።

2.ጾመ ሁዳዴ

በጥንት ጊዜ ገባሮች ለባለ ርስት የሚያርሱት መሬት ሁዳዴ ተብሎ ይጠራ ነበር። እኛም ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስን እያሰብን የምንጾመው በመሆኑ ጾመ ሁዳዴ ተብሏል።

3.የካሳ ጾም

አዳምና ሔዋን ከገነት የተባረሩት ለውርደት ሞት ለሲዖል ባርነት የበቁት በመብል ምክንያት ነው። በመብል ምክንያት የሞተውን የሰው ልጅ ጌታችን በፈቃዱ በፈጸመው ጾም ካሰው፤ መንፈሳዊ ረሃብን በረሃቡ ካሰለት። ስለዚህም የካሳ ጾም ተባለ።

4. የድል ጾም
አርዕስተ ኃጣውእ /ማቴ 4/ ድል የተነሱበት በመሆኑ የድል ጾም ተብሏል።
5. የመሸጋገሪያ ጾም
ጌታችን ከሕገ ኦሪት ወደ ሕገ ልቦና ሊያሸጋግረን የጾመው ጾም በመሆኑ የመሸጋገሪያ ጾም ተብሏል።
6.ጾመ አስተምህሮ
ጌታችን የጾመው ለትምህርት ነው። እርሱ መጾም ያለበት ሆኖ አይደለም። ስለዚህም ይህ ጾም ጾመ አስተምህሮ ይባላል።
7.የቀድሶተ ገዳም ጾም
ጌታችን ከከተማ ርቆ ከሰው ተለይቶ በመጾም ከከተማ ርቆ ከሰው ተለይቶ በብሕትውና መኖርን ቀድሶ የሰጠ በት፣ የመጥምቁ ዮሐንስና የነቢዩ ኤልያስን ገዳማዊነት የባረከበት በመሆኑ የቀድሶተ ገዳም ጾም ተብሏል።
8.የመዘጋጃ ጾም
ሕዝበ እሥራኤል የፋሲካውን በግ ከመመገባቸው በፊት ዝግጅት ያደርጉ ነበር። እኛም ትንሣኤን ከማክበራችን፣ ሥጋና ደሙን ከመቀበላችን በፊት በጾምና በጸሎት ዝግጅት የምናደርግበት በመሆኑ የመዘጋጃ ጾም ተብሏል።

ዓቢይ ጾም ስምንት ሳምንት ማለትም 55 ቀናት አሉት። ከእነዚህም ቀናት ውስጥ ሰባት ቅዳሜና ስምንት እሑዶች ይገኛሉ። አሥራ አምስት ቀናት ማለት ነው። እነዚህ ከጥሉላት እንጂ ከእህል ውኃ ስለማይጾሙ የሙሉ ቀናት ጾም አርባ ቀናት ብቻ ናቸዉ።

በሌላ መልኩ የመጀመሪያው ሳምንት ጾመ ሕርቃል የመጨረሻው ሳምንት ደግሞ ሰሙነ ሕማማት ይባላል። ሕርቃል በ614 ዓ.ም የቢዛንታይን ንጉሥ ነበር። ይህ ሳምንት በስሙ የተጠራበትም ምክንያት በዘመኑ ፋርሶች ኢየሩሳሌምን ወርረው የጌታን መስቀል ማርከው ወስደው ነበር። ምእመናን «ተዋግተህ አስመልስልን» አሉት። እርሱም «ሐዋርያት ነፍስ የገደለ መላ ዘመኑን ይጹም ብለዋል። ስለዚህ ይኸንን የዕድሜ ልክ ጾም ፈርቼ እንጂ ደስ ይለኛል» ሲል መለሰላቸው። እነርሱም «የአንድ ሰው ዕድሜ ቢኖር ሰባ ሰማኒያ ዘመን ነው። እኛ ተካፍለን እንጾምልሃለን» ስላሉት ፋርስ ዘምቶ መስቀሉን ከእነዚያ ነጥቆ ይዞ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሷል። መታሰቢያም እንዲሆን ይህን የጾም ሳምንት በቀኖና ውስጥ አስገቡት። ጾሙም ጾመ ሕርቃል ይባላል። ታሪኩ የመስቀል ፍቅር የተገለጠበት ታሪክ ነው። ሰሙነ ሕማማትን በቀጣዩ እንመለከታለን።

ሐዋርያት የጌታችንን መከራና ሞት እያሰቡ የጦሙት ነው። ያም ሆነ ይህ ሁሉም ከዓቢይ ጾም ጋር እንደመርገፍና እንደ እጂታ ስለተያያዘ ከዓቢይ ጾም ይቆጠራል። ዓቢይ ጾም መባሉ የጌታ ጾም ስለሆነና ታላላቅ የሰይጣን ፈተናዎች ድል የተነሱበት ጾም ስለሆነ ነው። ከዚህ በታች ደግሞ በዓቢይ ጾም ውስጥ የሚገኙትን ሰንበታት በዝርዝር እንመለከታለን።

የዐቢይ ጾም ሳምንታት፦
የቤተክርስቲያናችንን መዝሙር ንባቡን ከዜማው አስማምቶ አጠናቅሮ የተናገረው ኢትዮጵያዊ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በጾመ ድጓው በሁዳዴ ለሚገኙት እሑዶች ሁሉ የተለየ መዝሙር ሠርቶላቸዋል። በመዝሙሩ ውስጣዊ ምሥጢር መሠረትም እያንዳንዱ እሑድ ተሰይሞበታል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሥርዓትና በትውፊት የበለጸገች መሆኗ የታመነ ነው። ስፊ ሥርዓትና ትውፊት ያላት እንደመሆኗ መጠን የምታከብረው ሰንበትና በዓል፣ የምትጾመው ጾም፣ የምትጸልየው ጸሎት፣ የምትቆመው ማኅሌት በቂ ታሪክ ትውፊትና ሥርዓት አለው። ያለ ታሪክ ያለ ትውፊትና ሥርዓት የምትዘምረው መዝሙርና የምትጸልየው ጸሎት፣ የምትጾመው ጾም የምታከብረው ሰንበትና በዓል የለም። በዚህም ሁኔታ በጾመ ሁዳዴ የምትጾመው ጾም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ጾም እንደመሆኑ መጠን በዚሁ የጾም ወራት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም በዘመነ ሥጋዌው ለሠራቸው የተአምራትና የትምህርት ሥራዎች መታሰቢያ በዓል በማድረግ ለእያንዳንዱ ሰንበት ስም በመስጠት በስሙ አንጻር የበዓሉን ታሪክ በመከተል ታመሰግናለች፤ ትዘምራለች፤ ትጸልያለች፤ ትቀድሳለች።

በዚህ ዓይነት የመጀመሪያው ሰንበት ማለት የቅበላ እሑድና ሳምንቱ ዘወረደ ወይም ሙሴኒ ሲባል ሁለተኛው ሰንበትና ሳምንቱ ቅድስት ይባላል። እንደዚሁም ሦስተኛው ሰንበትና ሳምንቱ ምኩራብ በመባል ሲጠራ አራተኛው ሰንበትና ሳምንቱ መጻጉዕ ተብሎ ተሰይሟል። የአምስተኛው ሰንበትና ሳምንቱ /ከግማሽ ጾም በኋላ ጀምሮ ያለው ሳምንት/ ደብረ ዘይት ሲባል ስድስተኛው ሰንበትና ሳምንቱ ገብርኄር ይባላል። እንዲሁም ሰባተኛው ሰንበትና ሳምንቱ ኒቆዲሞስ ሲባል ስምንተኛው ሰንበትና ሳምንቱ ሆሣዕና በመባል ይወቃል። ከዚህ በመቀጠል በቅደም ተከተላቸው እንመለከታለን።

## 1. ዘወረደ ወይም ሙሴኒ፦

የመጀመሪያውን ጾም የምንቀበልበት ሰንበት ወይም ቅበላ የተባለው እሑድ ዘወረደ ወይም ሙሴኒ የተባለበት ምክንያት በዚህ ዕለት ዋዜማ የሚዘመረው ማኅትው በመዋዕለ ጾሙ ጠቅላላ የሚዘመረው የጾመ ድጓው መጀመሪያ «ዘወረደ እምላዕሉ አይሁድ ሰቀሉ» ብሎ ስለሚጀመር በዚህ ማኅትው የተሰየመ ነው። «ዘወረደ እምላዕሉ አይሁድ ሰቀሉ» ማለትም ከላይ የወረደውን /አምላክ/ አይሁድ ሰቀሉት ማለት ስለሆነ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የዕርገቱን የስቅለቱን የአዳኝነቱን መታሰቢያ የያዘ ነው። /ዮሐ 1:9-11፣ 3:13-21/። ሳምንቱ ሙሴኒ የተባለበትም ምክንያት በዚሁ ሳምንት መጀመሪያ የሰኞ ዕዝል «ከመዝ ይቤ ሙሴ ፀዓቱ እምትእይንት» «ሙሴ ከከተማ መውጣቱ እንደዚህ ነው አለ» ስለሚል እንደዚሁም የዚሁ ዕለት ማለት የሰኞ

አቡን «ሙሴኒ ይቤ በውስተ አሪት ምድር ሰናይት» እያለ የሙሴን ታሪክ ስለሚያጠቃቅስ ሳምንቱ ሙሴኒ ተባለ። ነቢያትም አርባ አርባ ቀን ጾመው ከአለፉ በኋላ የሙሴ ሕግና ትንቢተ ነቢያት ፈጻሚ የሆነው አምላካችን እንደ እነሱ 40 ቀንና 40 ሌሊት መጾሙን የሚያስታውስ ነው። /ዘፀ 24. 18፤ 1ኛ ነገ 19፣8፤ ማቴ 4. 1-4/።

በገባሬ ሰናዩ ዲያቆን ዕብ 13፡7-17፡- «የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው። ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ። ልባችሁ በጸጋ ቢጸና መልካም ነው እንጂ በመብል አይደለም፤ በዚህ የሚሠሩባት አልተጠቀሙምና። መሠዊያ አለን፣ ከእርሱም ሊበሉ ድንኳኒቱን የሚያገለግሉ መብት የላቸውም። ሊቀካህናት ስለ ኃጢአት ወደ ቅድስት የእንስሶችን ደም ያቀርባልና፤ ሥራቸው ግን ከሰፈሩ ውጭ ይቃጠላል። ስለዚህ ኢየሱስ ደግሞ በገዛ ደሙ ሕዝቡን እንዲቀድስ ከበር ውጭ መከራን ተቀበለ። እንግዲህ ነቀፌታውን እየተሸከምን ወደ እርሱ ወደ ሰፈሩ ውጭ እንውጣ፤ በዚህ የምትኖር ከተማ የለችምና፣ ነገር ግን ትመጣ ዘንድ ያላትን እንፈልጋለን። እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት፣ ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ ለእርሱ እናቅርብለት። ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና።

ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ። እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው፣ ይህንኑ በደስታ እንጂ በኃዘን እንዲያደርጉት፣ ይህ የማይጠቅማችሁ ነበርና ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ።»

በንፍቅ ዲያቆን: ያዕ 4፡6-17 «ስለዚህ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፣ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል። እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ፤ ወደ እናንተም ይቀርባል። እናንተ ኃጢአተኞች እጆቻችሁን አንጹ፤ ሁለት አሳብም ያላችሁ እናንተ፣ ልባችሁን አጥሩ ተጨነቁና እዘኑ አልቅሱም፤ ሳቃችሁ ወደ 'ዘን ደስታችሁም ወደ ትካዜ ይለወጥ። በጌታ ፊት ራሳችሁን አዋርዱ ከፍ ከፍም ያደርጋችኋል።

ወንድሞች ሆይ እርስ በርሳችሁ አትተማሙ። ወንድሙን የሚያማ በወንድሙም የሚፈርድ ሕግን ያማል በሕግም ይፈርዳል፤ በሕግም ብትፈርድ ፈራጅ ነህ እንጂ ሕግን አድራጊ አይደለህም። ሕግን የሚሰጥና የሚፈርድ አንድ ነው፤ እርሱም ሊያድን ሊያጠፋም የሚችል ነው፤ በሌላው ግን የምትፈርድ አንተ ማን ነህ?
አሁንም ዛሬ ወይም ነገ ወደዚህ ከተማ እንሄዳለን በዚያም ዓመት እንኖራለን እንነግድማለን እናተርፍማለን የምትሉ እናንተ ተመልከቱ ነገ የሚሆነውን አታውቁምና። ሕይወታችሁ ምንድን ነው? ጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፏሎት ናችሁና። በዚህ ፈንታ:- ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ማለት ይገባችኋል። አሁን ግን በትዕቢታችሁ ትመካላችሁ፤ እንደዚህ ያለ ትምክህት ሁሉ ክፉ ነው። እንግዲህ በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው።»

በንፍቅ ቄስ: የሐዋ.ሥራ 25፡13-27፡- «ከጥቂት ቀንም በኋላ ንጉሡ አግጳ በርኒቄም ለፊስጦስ ሰላምታ እንዲያቀርቡ ወደ ቂሣሪያ ወረዱ። በዚያውም ብዙ ቀን ስለ ተቀመጡ ፊስጦስ የጳውሎስን ነገር ለንጉሡ እንዲህ ብሎ ገለጠ:- ፊልክስ አስሮ የተወው አንድ ሰው በዚህ አለ፤ በኢየሩሳሌምም ሳለሁ የካህናት አለቆችና የአይሁድ ሽማግሌዎች እፈርድበት ዘንድ እየለመኑ ስለ እርሱ አመለከቱኝ። እኔም ተከሳሹ በከሳሾቹ ፊት ለፊት ሳይቆም ለተከሰሰበትም መልስ ይሰጥ ዘንድ ፈንታ ሳያገኝ፣ ማንንም ቢሆን አሳልፎ መስጠት የሮማውያን ሥርዓት አይደለም ብዬ መለስሁላቸው። ስለዚህም በዚህ በተሰበሰቡ ጊዜ፣ ሳልዘገይ በማግሥቱ በፍርድ ወንበር ተቀምጬ ያንን ሰው ያመጡት ዘንድ አዘዝሁ። ከሳሾቹም በቆሙ ጊዜ እኔ ያሰብሁትን ክፉ ነገር ክስ ምንም አላመጡበትም፤ ነገር ግን ስለገዛ ሃይማኖታቸውና ጳውሎስ ሕያው ነው ስለሚለው ስለ ሞተው ኢየሱስ ስለ ተባለው ከእርሱ ጋር ይከራከሩ ነበር። እኔም ይህን ነገር እንዴት እንድመረምር አመንትቼ:- ወደ ኢየሩሳሌም ሄደህ በዚህ ነገር ከዚያ ልትፋረድ ትወዳለህን? አልሁት። ጳውሎስ ግን አውግስጦስ ቄሣር እስኪቆርጥ ድረስ እንዲጠበቅ ይግባኝ ባለ ጊዜ፣ ወደ ቄሣር እስክሰደው ድረስ ይጠበቅ ዘንድ አዘዝሁ። አግጳም ፊስጦስን:- ያንንስ ሰው እኔ ዳግም እኮ እሰማው ዘንድ እወድ ነበር አለው። እርሱም:- ነገ ትሰማዋለህ አለው። በነገውም አግጳና በርኒቄ በብዙ ግርማ መጥተው ከሻለቆችና ከከተማው ታላላቆች ጋር ወደ ፍርድ ቤት ገቡ፤ ፊስጦስም ባዘዘ ጊዜ ጳውሎስን አመጡት። ፊስጦስም አለ:- አግጳ ንጉሥ ሆይ እናንተም ከእኛ ጋር ያላችሁ ሰዎች ሁሉ ከእንግዲህ ወዲህ በሕይወት ይኖር ዘንድ እንዳይገባው እየጮኹ የአይሁድ ሕዝብ ሁሉ በኢየሩሳሌም በዚህም ስለ እርሱ የለመኑኝን ይህን ሰው ታዩታላችሁ ይልቁንም በፊትህ፣ ንጉሥ አግጳ ሆይ፣ አመጣሁት፤ እስረኛ ሲላክ የተከሰሰበትን ምክንያት ደግሞ አለማመልከት ሞኝነት መስሎኛልና።»

በገባሬ ሰናዩ ዲያቆን: መዝ 2፡11

- ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሃት
  ወተሐሰዩ ሎቱ በረዓድ
  አንዕዋ ለጥበብ ከመ ኢይትመዐዕ እግዚአብሔር

- ለእግዚአብሔር በፍርሃት ተገዙ
  በረዓድም ደስ ይበላችሁ።
  ተግሣጹን ተቀበሉ ጌታ እንዳይቆጣ

በገባሬ ሰናዩ ቄስ፡ ዮሐ 3፡10-25፡- «ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡- አንተ የእስራኤል መምህር ስትሆን ይህን አታውቅምን? እውነት እውነት እልሃለሁ፣ የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውንም እንመሰክራለን፣ ምስክራችንንም አትቀበሉትም ስለ ምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ ካላመናችሁ፣ ስለ ሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ? ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም፣ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው፡፡ ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል፡፡
በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፡፡ ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፣ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና፡፡ በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል፡፡ ብርሃንም ወደ ዓለም ስለመጣ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለወደዱ ፍርዱ ይህ ነው፡፡ ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና፣ ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም፤ እውነትን የሚያደርግ ግን ሥራው በእግዚአብሔር ተደርጎ እንደ ሆነ ይገለጥ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል፡፡
ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ወደ ይሁዳ አገር መጣ፣ በዚያም ከእነርሱ ጋር ተቀምጦ ያጠምቅ ነበር፡፡ ዮሐንስም ደግሞ በሳሌም አቅራቢያ በሄኖን በዚያ ብዙ ውኃ ነበርና ያጠምቅ ነበር፣ እየመጡም ይጠመቁ ነበር፤ ዮሐንስ ገና ወደ ወኅኒ አልተጨመረም ነበርና፡፡ ስለዚህም በዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና በአይሁድ መካከል ስለ ማንጻት ክርክር ሆነ፡፡»

## 2. ቅድስት

የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጾመ # የሚጀመርበት ሁለተኛው ሰንበት ቅድስት ተብሎ የሚጠራበት ምክንያት ከዚሁ ሰንበት ዋዜማ ጀምሮ የሚዘመረው ጾመ ድጓ ቀለሙ «ዛቲ ዕለት ቅድስት ይዕቲ» «ይች ቀን የተቀደሰች ናት» «ሰንበትየ ቅድስትየ እንተ አዕረፍኩ» «ያረፍኩባት ቅድስት ሰንበት ናት፡፡» «ቅዱሳነ ኩኑ እስመ አነሂ ቅዱስ አነ» «እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» አለ እግዚአብሔር «አብ ቀደሳ ለሰንበት» «አብ ሰንበትን አከበራት ቀደሳት» እያለ የሰንበትን ቅድስና እያነሣሣ ስለሚዘምር ይህ ሳምንት ቅድስት ተብሏል፡፡ ስያሜውም ሰንበት የዕረፍት ቀን እንድትሆን በኦሪትም በሐዲስም እግዚአብሔር የባረካት የቀደሳት ዕለት መሆኑዋን የሚያሳስብና እግዚአብሔር ቅዱስ እንደሆነ የፈጠረውም ሰውም ቅድስናን መያዝ የሚገባው መሆኑን የሚያሳስብ ነው፡፡ /ዘፍ 2፡3፣ ዘፀ. 20፡8-11፣ ዘሌ 19፡2-3፣ 1ጴጥ 1፡15-16/
1 ተሰ 4፡6-13 «አስቀድመን ደግሞ እንዳልናችሁና እንደመሰከርንላችሁ፣ ጌታ ስለዚህ ነገር ሁሉ የሚበቀል ነውና ማንም በዚህ ነገር አይተላለፍ ወንድሙንም አያታልል፡፡ ለርኩሰት ሳይሆን እግዚአብሔር በቅድስና ጠርቶናልና፡፡ እንግዲህ የሚጥል ሰውን የጣለ አይደለም፣ መንፈስ ቅዱስን በእናንተ እንዲኖር የሰጠውን እግዚአብሔርን ነው እንጂ፡፡
እናንተ ራሳችሁ እርስ በርሳችሁ ልትዋደዱ ከእግዚአብሔር ተምራችኋልና ስለ ወንድማማች መዋደድ ማንም ይጽፍላችሁ ዘንድ አያስፈልጋችሁም፤ እንዲሁ በመቄዶንያ ሁሉ ላሉት ወንድሞች ሁሉ ታደርጋላችሁና፡፡ ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ከፊት ይልቅ ልትበዙ፣ በጸጥታም ትኖሩ ዘንድ በአገባብ እንድትመላለሱ፣ አንዳችም እንዳያስፈልጋችሁ በእጃችሁ ልትሠሩ እንለምናችኋለን፡፡ ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ አንቀላፍተው ስላሉት ታውቁ ዘንድ እንወዳለን፡፡»
1 ጴጥ 1፡13-25 «ስለዚህ የልቦናችሁን ወገብ ታጥቃችሁና በመጠን እየኖራችሁ፣ ኢየሱስ ክርቶስ ሲገለጥ የምታገኙትን ጸጋ ፈጽማችሁ ተስፋ አድርጉ፡፡ እንደሚታዘዙ ልጆች ባለማወቃችሁ አስቀድሞ የኖራችሁበትን ምኞት አትከተሉ፡፡ ዳሩ ግን «እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ» ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ፡፡ ለሰው ፊትም ሳያደላ በእያንዳንዱ ላይ እንደሥራው የሚፈርደውን አባት ብላችሁ ብትጠሩ በእንግድነታችሁ ዘመን በፍርሃት ኑሩ፡፡ ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደ ተዋጃችሁ ታውቃላችሁ ፡፡ ዓለም ሳይፈጠር እንኳ አስቀድሞ ታወቀ፣ ነገር ግን እምነታችሁና ተስፋችሁ በእግዚአብሔር ይሆን ዘንድ፣ ከሙታን ባስነሣው ክብርንም በሰጠው በእግዚአብሔር በእርሱ ስለምታምኑ ስለ እናንተ በዘመኑ መጨረሻ ተገለጠ፡፡
ለእውነት እየታዘዛችሁ ግብዝነት ለሌለበት ለወንድማማች መዋደድ ነፍሳችሁን አጽንታችሁ እርስ በርሳችሁ ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ፡፡ ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፣ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ፡፡
ሥጋ ሁሉ እንደሣር ክብሩም ሁሉ እንደ ሣር አበባ ነውና፤ ሣሩ ይጠወልጋል አበባውም ይረግፋል፤ የጌታ ቃል ግን ለዘላለም ይኖራል፡፡ በወንጌልም የተሰበከላችሁ ቃል ይህ ነው፡፡»
የሐዋ.ሥራ 10፡17-30 «ጴጥሮስም ስላየው ራእይ ምን ይሆን? ብሎ በልቡ ሲያመነታ፣ እነሆ ቆርኔሌዎስ የላካቸው ሰዎች ስለ ስምዖን ቤት ጠይቀው ወደ ደጁ ቀረቡ፤ ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው፡- ጴጥሮስ የተባለው ስምዖን በዚህ እንግድነት ተቀምጦአልን? ብለው ይጠይቁ ነበር፡፡ ጴጥሮስም ስለ ራእዩ ሲያወጣ ሲያወርድ ሳለ፣ መንፈስ፡- እነሆ ሦስት ሰዎች ይፈልጉሃል፤ ተነሥተህ ውረድ፣ እኔም ልኬአቸዋለሁና ሳትጠራጠር ከእነርሱ ጋር ሂድ አለው፡፡ ጴጥሮስም ወደ ሰዎቹ ወርዶ እነሆ የምትፈልጉኝ እኔ ነኝ፤ የመጣችሁበትስ

ምክንያት ምንድር ነው? አላቸው። እነርሱም፡- ጻድቅ ሰው እግዚአብሔርንም የሚፈራ በአይሁድም ሕዝብ ሁሉ የተመሰከረለት የመቶ አለቃ ቆርኔሌዎስ ወደ ቤቱ ያስመጣህ ዘንድ ከአንተም ቃልን ይሰማ ዘንድ ከቅዱስ መልአክ ተረዳ አሉት። እርሱም ወደ ውስጥ ጠርቶ እንግድነት ተቀበላቸው።
በነገውም ተነሥቶ ከእነርሱ ጋር ወጣ፣ በኢዮጴም ከነበሩት ወንድሞች አንዳንዶቹ ከእርሱ ጋር አብረው ሄዱ በነገውም ወደ ቂሣርያ ገቡ፤ ቆርኔሌዎስም ዘመዶቹንና የቅርብ ወዳጆቹን በአንድነት ጠርቶ ይጠባበቃቸው ነበር። ጴጥሮስም በገባ ጊዜ ቆርኔሌዎስ ተገናኝቶ ከእግሩ በታች ወደቀና ሰገደለት። ጴጥሮስ ግን ተነሣ እኔ ራሴ ደግሞ ሰው ነኝ ብሎ አስነሣው። ከእርሱም ጋር እየተነጋገረ ገባ፣ ብዙዎችም ተከማችተው አግኝቶ፡- አይሁዳዊ ሰው ከሌላ ወገን ጋር ይተባበር ወይም ይቃረብ ዘንድ እንዳልተፈቀደ እናንተ ታውቃላችሁ፤ ለእኔ ግን እግዚአብሔር ማንንም ሰው ርኩስና የሚያስጸይፍ ነው እንዳልል አሳየኝ፤ ስለዚህም ደግሞ ብትጠሩኝ ሳልከራከር መጣሁ። አሁንም በምን ምክንያት አስመጣችሁኝ? ብዬ እጠይቃችኋለሁ አላቸው። ቆርኔሌዎስም እንዲህ አለው፡- በዚች ሰዓት የዛሬ አራት ቀን የዘጠኝ ሰዓት ጸሎት በቤቴ እጸልይ ነበር።»

መዝ 95:5

- እግዚአብሔርሰ ሰማያተ ገብረ
  አሚን ወሰናይት ቅድሜሁ
  ቅድሳት ወዕበየ ስብሐት ውስተ መቅደሱ

- እግዚአብሔር ግን ሰማያትን ሠራ።
  ምስጋናና ውበቱ በፊቱ
  ቅዱስነትና ግርማ በመቅደሱ ውስጥ ናቸው።

ማቴ 6:16-25 «ስትጦሙም፣ እንደግብዞች አትጠውልጉ፤ እንደጦመኛ ሊታዩ ፊታቸውን ያጠፋሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፣ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ስትጦም፣ በስውር ላለው አባትህ እንጂ እንደ ጦመኛ ለሰዎች እንዳትታይ ራስህን ተቀባ ፊትህንም ታጠብ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ያስረክብሃል።
ብልና ዝገት በሚያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በሚሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፤ ነገር ግን ብልም ዝገትም በማያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በማይሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፤ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና። የሰውነት መብራት ዓይን ናት። ዓይንህ እንግዲህ ጤናማ ብትሆን ሰውነትህ ሁሉ ብሩህ ይሆናል፤ ዓይንህ ግን ታማሚ ብትሆን ሰውነትህ ሁሉ የጨለመ ይሆናል። እንግዲህ በአንተ ያለው ብርሃን ጨለማ ከሆነ፣ ጨለማውስ እንዴት ይበረታ።
ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም። ስለዚህም እላችኋለሁ ስለ ነፍሳችሁ በምትበሉትና በምትጠጡት፣ ወይም ስለሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ።»

## 3. ምኩራብ

ሦስተኛው ሰንበት ምኩራብ ተብሎ የተሰየመበት ምክንያት በዚሁ ዕለት የሚዘመረው ጾመ ድጓ ከዋዜማው ጀምሮ እስከ ሰላሙ ድረስ በዕለተ ሰንበት «ቦአ ኢየሱስ ምኩራበ አይሁድ» «ኢየሱስ በሰንበት ቀን ወደ አይሁድ ምኩራብ ገባ» እያለ ኢየሱስ በአይሁድ ምኩራብ ማስተማሩን እየጠቃቀሰና እያነሣሣ ስለሚዘምር ይህን ሰንበት ለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምኩራብ እየገባ ለማስተማሩና በምኩራብ የሚሸጡ የሚለውጡ ነጋዴዎችን ለማስወጣቱ ቤተ መቅደሱን ለማስከበሩ መታሰቢያ ሆኖ ስለተሰጠ ነው። የዚህም በዓል ታሪክ ዝርዝር ሁኔታው በማቴዎስ ወንጌል ምዕ 21:12-13 ተጠቅሷል።
ቈላስ 2:16-23 «እንግዲህ በመብል ወይ በመጠጥ ወይም ስለ በዓል ወይም ስለ ወር መባቻ ወይም ስለሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና፣ አካሉ ግን የክርስቶስ ነው። ትሕትናንና የመላእክትን አምልኮ እየወደደ፣ ባላየውም ያለፈቃድ እየገባ፣ በሥጋዊም አእምሮ በከንቱ እየታበየ ማንም አይፍረድባችሁ፤ እንደዚህ ያለ ሰው ራስ ወደሚሆነው አይጠጋም፣ ከእርሱም አካል ሁሉ በጅማትና በማሰሪያ ምግብን እየተቀበለ እየተጋጠመም፣ እግዚአብሔር በሚሰጠው ማደግ ያድጋል። ከዓለማዊ ከመጀመሪያ ትምህርት ርቃችሁ ከክርስቶስ ጋር ከሞታችሁ፣ እንደሰው ሥርዓትና ትምህርት፡- አትያዝ አትቅመስ፣ አትንካ ለሚሉት ትእዛዛት በዓለም ሁሉ እንደምትኖሩ ስለምን ትገዛላችሁ? እነዚህ ሁሉ በመደረግ ሊጠፉ ተወስነዋልና። ይህ እንደገዛ ፈቃድህ በማምለክና በትሕትና ሥጋንም በመጨቈን ጥበብ ያለው ይመስላል፣ ነገር ግን ሥጋ ያለ ልክ እንዳይጠግብ ለመከልከል ምንም አይጠቅምም።»

ያዕ 2:14-26 « ወንድሞቼ ሆይ፣ እምነት አለኝ የሚል፣ ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን? ወንድም ወይም እኅት ራቁታቸውን ቢሆኑ የዕለት ምግብንም ቢያጡ፣ ከእናንተ አንዱም በደህና ሂዱ፣ እሳት ሙቁ፣ ጥገቡም ቢላቸው ለሰውነት ግን የሚያስፈልጉትን ባትሰጡአቸው ምን ይጠቅማቸዋል? እንደዚሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው።

ነገር ግን አንድ ሰው አንተ እምነት አለህ እኔም ሥራ አለኝ፤ እምነትህን ከሥራህ ለይተህ አሳየኝ፣ እኔም እምነቴን በሥራዬ አሳይሃለሁ ይላል። በእግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል። አንተ ከንቱ ሰው፣ እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህን? አባታችን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን በመሠዊያው ባቀረበ ጊዜ በሥራ የጸደቀ አልነበረምን? እምነት ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደ ነበረ፣ በሥራም እምነት እንደተፈጸመ ትመለከታለህን? መጽሐፍም አብርሃምም እግዚአብሔር አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት ያለው ተፈጸመ፤ የእግዚአብሔርም ወዳጅ ተባለ። ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ። እንደዚሁም ጋለሞይቱ ረዓብ ደግሞ መልእክተኞቹን ተቀብላ በሌላ መንገድ በሰደደቻቸው ጊዜ በሥራ አልጸደቀችምን? ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።»

የሐዋ.ሥራ 10፡1-9 « በቂሣርያም ኢጣሊቄ ለሚሉት ጭፍራ የመቶ አለቃ የሆነው ቆርኔሌዎስ የሚሉት አንድ ሰው ነበር። እርሱም ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር እግዚአብሔርን የሚያመልክና የሚፈራ ለሕዝብም እጅግ ምጽዋት የሚያደርግ ወደ እግዚአብሔርም ሁልጊዜ የሚጸልይ ነበረ። ከቀኑም ዘጠኝ ሰዓት ያህል፡- ቆርኔሌዎስ ሆይ የሚለው የእግዚአብሔር መልአክ ወደ እርሱ ሲገባ በራእይ በግልጥ አየው እርሱም ትኩር ብሎ ሲመለከተው ደንግጦ ጌታ ሆይ ምንድር ነው? አለ። መልአኩም አለው፡- ጸሎትህና ምጽዋትህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ እንዲሆን ዐረገ። አሁንም ወደ ኢዮጴ ሰዎችን ልከህ ጴጥሮስ የሚባለውን ስምዖንን አስመጣ። እርሱ ቤቱ በባሕር አጠገብ ባለው በቁርበት ፋቂው በስምዖን ዘንድ እንግድነት ተቀምጦአል፤ ልታደርገው የሚገባህን እርሱ ይነግርሃል። የተናገረውም መልአክ በሄደ ጊዜ ከሎሌዎቹ ሁለቱን፣ ከሚያገለግሉትም ጭፍሮቹ እግዚአብሔርን የሚያመልክ አንዱን ወታደር ጠርቶ፣ ነገሩን ሁሉ ተረከላቸው ወደ ኢዮጴም ላካቸው። እነርሱም በነገው ሲሄዱ ወደ ከተማም ሲቀርቡ፣ ጴጥሮስ በስድስት ሰዓት ያህል ይጸልይ ዘንድ ወደ ጣራው ወጣ።

መዝ 68፡9

- እስመ ቅንዐተ ቤትከ በልዐኒ
  ትዕይርቶሙ ለእለ ይትዔየሩከ ወድቀ ላዕሌየ
  ወቀጻዕክዋ በጾም ለነፍስየ።

- የቤትህ ቅንዓት በልታኛለችና
  የሚሰድቡህም ስድብ በላዬ ወድቆአልና
  ነፍሴን በጾም አስመረርሁአት።

ዮሐ 2፡12-25 «ከዚህ በኋላ ከእናቱና ከወንድሞቹ ከደቀመዛሙርቱም ጋር ወደ ቅፍርናሆም ወረደ፣ በዚያም ጥቂት ቀን ኖሩ። የአይሁድ ፋሲካም ቀርቦ ነበር ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። ወደ መቅደስም በሬዎችንና በጎችን ርግቦችንም የሚሸጡትን ገንዘብ ለዋጮችንም ተቀምጠው አገኘ፤ የገመድም ጅራፍ አበጅቶ ሁሉን በጎችንም በሬዎችንም ከመቅደስ አወጣቸው፣ የለዋጮችንም ገንዘብ አፈሰሰ፣ ገበታዎቻቸውንም ገለበጠ፣ ርግብ ሻጪዎችንም ይህን ከዚህ ውሰዱ። የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት አላቸው። ደቀ መዛሙርቱም የቤትህ ቅናት ይበላኛል ተብሎ እንደተጻፈ አሰቡ። ስለዚህ አይሁድ መልሰው ይህን ስለምታደርግ ምን ምልክት ታሳየናለህ? አሉት። ኢየሱስም መልሶ ይህን ቤተመቅደስ አፍርሱት በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ አላቸው ስለዚህ አይሁድ ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ስድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር፣ አንተስ በሦስት ቀን ታነሣዋለህን? አሉት። እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተመቅደስ ይል ነበር። ስለዚህ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ደቀመዛሙርቱ ይህን እንደተናገረ አሰቡና መጽሐፍንና ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አመኑ።
በፋሲካ በዓልም በኢየሩሳሌም ሳለ፣ ያደረገውን ምልክት ባዩ ጊዜ ብዙ ሰዎች በስሙ አመኑ ነገር ግን ኢየሱስ ሰዎችን ሁሉ ያውቅ ነበር፤ ስለ ሰውም ማንም ሊመሰክር አያስፈልገውም ነበርና አይተማመናቸውም ነበር፣ ራሱ በሰው ያለውን ያውቅ ነበርና።»

## 4. መጻጉዕ

አራተኛው እሑድ መጻጉዕ የተባለበት ምክንያት በዚሁ ሰንበት የሚዘመረው ጾመ ድጓ ከዋዜማው ጀምሮ «አሕየዎ ኢየሱስ ለመጻጉዕ ለVwወ8 ክረtምተ ሐመ» «38 ዓመት ሽባ ሆኖ የታመመውን መጻጉዕን ኢየሱስ አዳነው» «እግዚእየአ አዝዝአ በቃልከአ የሐዬአ ቁልኤየአ ታሕተ ጠፈረ ቤትየ ኢይደልወከ በዊአ» «ጌታዬ በቃልህ እዘዝ ልጄ ይድናል። በቤቴ ጣርያ ሥር አንተ ልትገባ አይገባህም» አለው የመቶ አለቃው። «ከልሓ ዕውር በውስተ ፍኖት ወገሠጽዎ እለ ይመርሕዎ ከመ ያርምም ወአዕበየ ከሊሐ እንዘ ይብል ተሣሃለኒ እግዚእየ ወልደ ዳዊት ርድአኒ» «ጌታ በሚያልፍበት መንገድ አንድ ዕውር ፈውሰኝ» ብሎ ጮኸ የሚመሩት ሰዎች ዝም በል አሉት። ዕውሩ ግን እምቢ ብሎ «የዳዊት ልጅ ጌታ ይቅር በለኝ ዕርዳኝ» እያለ ጩኸቱን ቀጠለ። «ሰንበት አሚሃ አመ ይቤሎ ለመጻጉዕ ተንሥእ ንሣእ አራተከ ነሥአ አራቶ አተወ ቤቶ እስመ ፈወሰ ወልደ እግዚአብሔር በሰንበት ኢየሱስ መጻጉዕን ተነሥ አልጋህን ተሸከም ባለው ጊዜ ቀኑ ሰንበት ነበረ። መጻጉዕም አልጋውን ተሸክሞ ወደ ቤቱ ገባ የእግዚአብሔር ልጅ በሰንበት ፈውሶልና «በሰንበት ፈሰወ ዱያነ ወከሠተ አዕይንተ ዕውራን» «በሰንበት ድውያንን ፈወሰ የዕውራንንም ዓይኖች አበራ እያለ 38 ዓመት በአልጋ ቁራኛ

በደዌ ዳኛ ተይዞ ሲማቅቅ የኖረውን መጻጉዕንና ሌሎቹን በልዩ ልዩ ደዌ የተያዙትን ሕሙማን መፈወሱን በጠቀላላው ለምፅ ማንጻቱን ዕውር ማብራቱን ሐንካሳን ማርታቱን ልምሾዎችን ማዳኑን አጋንንትን ማውጣቱን እየጠቃቀሰና እያነሣሣ ስለሚዘምር ዕለቱና ሳምንቱ መጻጉዕ ተብሏል።
ስለዚህም ይህ ሰንበት የሕሙማን ፈውስ መታሰቢያ ዕለት ነው ማለት ይቻላል። ለዚህ ዕለተ ሰንበት መታሰቢያነት የተሰጠው የመጻጉዕንና የሌሎችንም ሕሙማን ፈውስ የሚመለከተውን ታሪክ የምናገኘው ቀጥሎ በተጠቀሱት የወንጌል ክፍሎች ነው። ማቴ 4:24-26፣ 8:2-34፣ 14:14-36፣ 10:46-52፣ ሉቃስ 6:6-19፣ 11:14-23፣13:10-32፣ 18:35-43 ዮሐ 5:5-18፣ 9:1-33/ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ምዕራፎችና ቁጥሮች ብንመለከት የመጻጉዕንና የሌሎቹን ሕሙማን ሁሉ ደኅንነት ታሪክ ማግኘት እንችላለን። የሰንበቱም ስያሜ ልብ ወለድ አጠራር ሳይሆን በዚህ ዓይነት የቅዱሳት መጻሕፍትን ምሥጢርና የጸመ ድጓውን ይትበሀል ተከትሎ የተሰየመ መሆኑን እናስገነዝባለን።
ገላ 5:1-26 «በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፣ እንግዲህ ቁሙ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ። እነሆ እኔ እላችኋለሁ ብትገረዙ ክርስቶስ ምንም አይጠቅማችሁም። ሕግንም ሁሉ እንዲፈጽም ግድ አለበት ብዬ ለሚገረዙ ሁሉ ለእንዳንዶች ደግሜ እመክራለሁ። በሕግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከጸጋው ወድቃችኋል። እኛ በመንፈስ ከእምነት የጽድቅን ተስፋ እንጠባበቃለንና በክርስቶስ ኢየሱስ ትሮጡ ነበር፣ ለእውነት እንዳትታዘዙ ማን ከለከላችሁ? ይህ ማባበል ከሚጠራችሁ አልወጣም። ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ ያቦካል። የተለየ ነገር ከቶ እንዳታስቡ እኔ በጌታ ስለ እናንተ ታምኜአለሁ፣ የሚያናውጣችሁ ማንም ቢኖር ግን ፍርዱን ሊሸከም ነው። ነገር ግን ወንድሞች ሆይ፣ እኔ ገና እስከ አሁን መገረዝ ብሰብክ እስከ አሁን ድረስ ለምን ያሳድዱኛል? እንኪያስ የመስቀል ዕንቅፋት ተወግዶአል። የሚያውኩአችሁ ይቆረጡ። ወንድሞች ሆይ በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ። ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈጸማልና፣ እርሱም ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የሚል ነው። ነገር ግን እርስ በርሳችሁ ብትነካከሱና ብትበላሉ እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ።
ነገር ግን እላለሁ፣ በመንፈስ ተመላለሱ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ። ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስንም በሥጋ ላይ ይመኛልና እነዚህ እርስ በርሳቸው ይቃወማሉ። ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም። በመንፈስ ብትመሩ ግን ከሕግ በታች አይደላችሁም። የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው። እርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ምዋርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንዓት፣ ቁጣ፣ አድመኛነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፣ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርሱም። የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የዋሃት፣ ራስን መግዛት ነው። እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም። የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ። በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለሳለን። እርስ በርሳችን እየተነሣሣንና እየተቀናናን በከንቱ አንመካ።»
ያዕ 5:14-20 «ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ቀሳውስት ወደ እርሱ ይጥራ፣ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት። የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሳዋል፣ ኃጢአትንም ሠርቶ እንደሆነ ይሰረይለታል። እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ፣ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ሰው ይጸልይ። የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች። ኤልያስ እንደ እኛ የሆነ ሰው ነበረ ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፣ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም። ሁለተኛም ጸለየ ሰማዩም ዝናብን ሰጠ ምድሪቱም ፍሬዋን አበቀለች።
ወንድሞች ሆይ ከእናንተ ማንም ከእውነት ቢስት አንዱም ቢመልሰው፣ ኃጢአተኛን ከተሳሳተበት መንገድ የሚመልሰው ነፍሱን ከሞት እንዲያድን፣ የኃጢአትንም ብዛት እዲሸፍን ይወቅ።
ሐዋ 3:1-12 «ጴጥሮስና ዮሐንስም በጸሎት ጊዜ በዘጠኝ ሰዓት ወደ መቅደስ ይወጡ ነበር። ወደ መቅደስም ከሚገቡት ምጽዋት ይለምን ዘንድ ሰዎች ተሸክመው መልካም በሚሉአት በመቅደስ ደጅ በየቀኑ ያስቀምጡት የነበሩ ከእናቱ ማኅጸን ጀምሮ አንካሳ የሆነ አንድ ሰው ነበር። እርሱም ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ መቅደስ ሊገቡ እንዳላቸው ባየ ጊዜ ምጽዋትን ለመናቸው። ጴጥሮስም ከዮሐንስ ጋር ትኩር ብሎ ወደ እርሱ ተመልክቶ ወደ እኛ ተመልከት አለው። እርሱም አንድ ነገር ከእነርሱ እንዲቀበል ሲጠብቅ ወደ እነርሱ ተመለከተ። ጴጥሮስ ግን ብርና ወርቅ የለኝም፣ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፣ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነስና ተመላለስ አለው። በቀኝ እጁም ይዞ አስነሣው፣ በዚያን ጊዜም እግሩና ቁርጭምጭምቱ ጸና ወደ ላይ ዘሎም ቆመ ይመላለስም ጀመር። እየተመላለሰም እየዘለለም እግዚአብሔርንም እያመሰገነ ከእነርሱ ጋር ወደ መቅደስ ገባ። ሕዝቡም ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ሲመላለስ አዩት፣ መልካምም በሚሉአት በመቅደስ ደጅ ስለምጽዋት ተቀምጦ የነበረው እርሱ እንደሆነ አወቁት፣ በእርሱም ከሆነው የተነሣ መደነቅና መገረም ሞላባቸው።
እርሱም ጴጥሮስና ዮሐንስን ይዞ ስለ ሕዝቡ ሁሉ እየተደነቁ የሰሎሞን ደጅ መመላለሻ በሚለው አብረው ወደ እነርሱ ሮጡ። ጴጥሮስም አይቶ ለሕዝቡ እንዲህ ሲል መለሰ:- የእሥራኤል ሰዎች ሆይ በዚህ ስለምን ትደነቃላችሁ? ወይስ በገዛ ኃይላችን ወይስ እግዚአብሔርን በመፍራታችን ይህ ይመላለስ ዘንድ እንዳደረግነው ስለምን ትኩር ብላችሁ ታዩናላችሁ?»
መዝ 40:3

- እግዚአብሔር ይረድኦ ውስተ ዐራተ ሕማሙ
  ወይመይጥ ሎቱ ኲሎ ምስካቤሁ እምደዌሁ
  አንሰ እቤ እግዚኦ ተሣሃለኒ።

- እግዚአብሔር በደዌው አልጋ ላይ ሳለ ይረዳዋል። 
መኝታውን ሁሉ በበሽታው ጊዜ ያነጥፍለታል
እኔስ አቤቱ ማረኝ።

ዮሐ 5፡1-25 «ከዚህ በኋላ የአይሁድ በዓል ነበረ፣ ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ። በኢየሩሳሌምም በበጎች በር አጠገብ በዕብራይስጥ ቤተ ሳይዳ የምትባል አንዲት መጠመቂያ ነበረች። አምስትም መመላለሻ ነበረባት፡ በእነዚህም ውስጥ የውኃውን መንቀሳቀስ እየጠበቁ በሽተኞችና ዕውሮች አንካሶችም ሰውነታቸውም የሰለለ ብዙ ሕዝብ ይተኙ ነበር። አንዳንድ ጊዜ የጌታ መልአክ ወደ መጠመቂያይቱ ወርዶ ውኃውን ያናውጥ ነበርና። እንግዲህ ከውኃው መናወጥ በኋላ በመጀመሪያ የገባ ከማናቸውም ካለበት ደዌ ጤናማ ይሆን ነበር።
በዚያም ከሠላሳ ስምንት ዓመት ጀምሮ የታመመ አንድ ሰው ነበረ። ኢየሱስ ይህን ሰው ተኝቶ ባየ ጊዜ፣ እስከ አሁን ብዙ ዘመን እንዲሁ እንደነበረ አውቆ ልትድን ትወዳለህን? አለው። ድውዩም ጌታ ሆይ ውኃው በተናወጠ ጊዜ በመጠመቂያይቱ ውስጥ የሚያኖረኝ ሰው የለኝም ነገር ግን እኔ ስመጣ ሳለሁ ቀድሞ ይወርዳል ብሎ መለሰለት። ኢየሱስ ተነሣና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ አለው።
ያም ቀን ሰንበት ነበር ። ስለዚህ አይሁድ የተፈወሰውን ሰው ሰንበት ነው አልጋህንም ልትሸከም አልፈቀደልህም አሉት ። እርሱ ግን ያዳነኝ ያ ሰው አልጋህን ተሸክመህ ሂድ አለኝ ብሎ መለሰላቸው። እነርሱም አልጋን ተሸክመህ ሂድ ያለው ሰው ማነው? ብለው ጠየቁት። ዳሩ ግን በዚህ ስፍራ ሕዝብ ስለ ነበሩ ኢየሱስ ፈቀቅ ብሎ ነበርና የተፈወሰው ሰው ማን እንደሆን አላወቀም። ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በመቅደስ አገኘውና እነሆ ድነሃል። ከዚህ የሚብስ እንዳይደርስብህ ወደፊት ኃጢአት አትሥራ አለው። ሰውየውም ሄዶ ያዳነው ኢየሱስ እንደሆነ ለአይሁድ ነገረ። ስለዚህም በሰንበት ይህን ስላደረገ አይሁድ ኢየሱስን ያሳድዱት ነበር። ሊገድሉምት ይፈልጉት ነበር። ኢየሱስ ግን አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል እኔም ደግሞ እሠራለሁ ብሎ መለሰላቸው። እንግዲህ ሰንበትን ስለሻረ ብቻ አይደለም ነገር ግን ደግሞ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ ስለዚህ አይሁድ ሊገድሉት አብዝተው ይፈልጉት ነበር።
ስለዚህ ኢየሱስ መለሰ እንዲህም አላቸው፡- እውነት እውነት እላችኋለሁ አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም። ያ የሚያደርገውን ሁሉ ያሳየዋል እናንተም ትደነቁ ዘንድ ከዚህ የሚበልጥ ሥራ ያሳየዋል። አብ ሙታንን እንደሚያስነሣ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው እንዲሁ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል። ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም። ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም። እውነት እውነት እላችኋለሁ። ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው። ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም። እውነት እውነት እላችኋለሁ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምጽ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል እርሱም አሁን ነው። የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ።»

## 5. ደብረዘይት

የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጾም አማካይ ሰንበት ወይም እኩል ጾም ላይ የሚውለው እሑድና ሳምንቱ ደብረዘይት የተባለበት ምክንያት ከዚሁ ሰንበት ዋዜማ ጀምሮ የሚዘመረው ጾመ ድጓ «እንዘይነብር እግዚእነ ውስተ ደብረ ዘይት ቀርቡ ኀቤሁ ኵሎሙ አርዳኢሁ በዕለተ ሰንበት ወይቤልዎ ንግረነ በምንት ይከውን ተአምሪሁ ለምጽአትከ ወለኀልቀተዓለም፡- ጌታችን በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ በዕለተ ሰንበት ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ወደ እርሱ ቀረቡና የመምጣትህ ምልክቱ የዓለምስ ማለፍ ምልክቱ በምን ይሆናል? ንገረን አሉት። «እንዘይነብር እግዚእነ ውስተ ደብረ ዘይት ወይቤሎሙ ለአርዳኢሁ ዑቁኬ ኢያስሕቱክሙ.... እምበለስ አእምሩ አምሳሊሁ ከመ በጽሐ ጊዜሁ ለማዕረር....ሰማይ ወምድር የ'ልፍ ወቃልየሰ ኢየ'ልፍ፡- ጌታችን በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ ለደቀ መዛሙርቱ እንዳያስቷችሁ ተጠንቀቁ ምጽአት እንደደረሰ ምሳሌውን/ምልክቱን/ ከበለስ እወቁ ሰማይ ከምድር ጋር ያልፋል ቃሌ ግን አያልፍም አላቸው» እያለ ጌታ በደብረ ዘይት ምሥጢረ ምጽአቱንና የዓለም ኅልፈትን ነገር ለማስተማሩና ከሐሰተኞች ነቢያት እንዲጠበቁ ለማስጠንቀቁ መታሰቢያ ሆኖ ስለተሰጠ ነው። የዚህም በዓል ታሪክ ዝርዝር ሁኔታው በማቴዎስ ወንጌል ምዕ 24 ቁ 1 እስከ መጨረሻው በማርቆስ ወንጌል ምዕ 13ቁጥር 1 እስከ መጨረሻው በሉቃስ ወንጌል ምዕ 14 ቁጥር 5 እስከ መጨረሻው ተጽፎ ይገኛል። ደብረ ዘይት በኢየሩሳሌም ምሥራቅ የሚገኝ ተራራ ነው። ጌታ በዚህ ዳግመኛ የመምጣቱን ትምህርት እንዳስተማረ ሁሉ ያረገውም በዚያ ተራራ ነው።
1ተሰ 4÷13-18 «ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ተስፋ እንደሌላቸው እንደሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ አንቀላፍተው ስላሉት ታውቁ ዘንድ እንወዳለን። ኢየሱስ እንደሞተና እንደተነሳ ካመንን እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና። እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉቱን አንቀድምም። ጌታ ራሱ በትዕዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፤ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሳሉ። ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን። ስለዚህ እርስ በእርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ።»
2ጴጥ3÷7-15 «አሁን ያሉ ሰማያትና ምድር ግን እግዚአብሔርን የማያመልኩት ሰዎች እስከሚጠፉበት እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ተጠብቀው በዚያ ቃል ለእሳት ቀርተዋል። እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን እንደሆነ ይህን አንድ ነገር አትርሱ። ለአንዳንዶቹ

የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለተስፋ ቃሉ አይዘገይም። ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፉ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሳል። የጌታ ቀን ግን እንደ ሌባ ሆኖ ይመጣል። በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፤ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይቀልጣል። ምድርም በእርስዋም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል። ይህ ሁሉ እንዲህ የሚቀልጥ ከሆነ የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት እየጠበቃችሁና እያስቸኰላችሁ በቅዱስ ኑሮ እግዚአብሔርንም በመምሰል እንደምን ልትሆኑ ይገባችኋል? ስለዚያ ቀን ሰማያት ተቃጥለው ይቀልጣሉ፤ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይፈታል፤ ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን።
ስለዚህ ወዳጆች ሆይ ይህን እየጠበቃችሁ ያለ ነውርና ያለ ነቀፋ ሆናችሁ በሰላም በእርሱ እንድትገኙ ትጉ የጌታችንም ትዕግሥት መዳናችሁ እንደሆነ ቁጠሩ።»
የሐዋ.ሥራ 24፥1-22 «ከአምስት ቀን በኋላም ሊቀ ካህናቱ ሐናንያ ከሽማግሌዎችና ጠርጠሉስ ከሚሉት ከአንድ ጠበቃ ጋር ወረደ፤ እነርሱም ስለ ጳውሎስ ለአገረ ገገዩ አመለከቱት። በተጠራም ጊዜ ጠርጠሉስ ይከሰው ዘንድ ጀመረ። እንዲህ እያለ «ክቡር ፊልክስ ሆይ በአንተ በኩል ብዙ ሰላም ስለምናገኝ ለዚህም ሕዝብ በአሳብህ በየነገሩ በየሥፍራውም መልካም መሻሻል ስለሚሆንለት፣ በፍጹም ምስጋና እንቀበለዋለን። ነገር ግን እጅግ እንዳላቆይህ በቸርነትህ በአጭሩ ትሰማኝ ዘንድ እለምንሃለሁ። ይህ ሰው በሽታ ሆኖ በዓለም ባሉት አይሁድ ሁሉ ሁከት ሲያስነሣ የመናፍቃን የናዝራውያን ወገን መሪ ሆኖ አግኝተነዋልና መቅደስንም ደግሞ ሊያረክስ ሲሞክር ያዝነው እንደ ሕጋችንም እንፈርድበት ዘንድ ወደድን ነገር ግን የሻለቃው ሉስዮስ መጥቶ በብዙ ኃይል ከእጃችን ወሰደው። ከሳሾቹንም ወደ አንተ ይመጡ ዘንድ አዘዘ። አንተም ራስህ እርሱን መርምረህ እኛ ስለምንከስበት ነገር ሁሉ ልታውቅ ትችላለህ። አይሁድም ደግሞ ይህ ነገር እንዲሁ ነው እያሉ ተስማሙ። ገዢውም በጠቀሰው ጊዜ ጳውሎስ መለሰ እንዲህ ሲል፦ ከብዙ ዘመን ጀምረህ ለዚህ ሕዝብ አንተ ፈራጅ እንደሆንህ አውቃለሁና ደስ እያለኝ ስለ እኔ ነገር እመልሳለሁ። እሰግድ ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም ከመጣሁ ከአሥራ ሁለት ቀን እንዳይበልጥ ልታውቀው ትችላለህ። ከአንድም ስንኳ ስነጋገር ወይም ሕዝብን ስሰበስብ በመቅደስ ቢሆን በምኩራብም ቢሆን በከተማም ቢሆን አላገኙኝም። አሁንም ስለሚከሱኝ ያስረዱህ ዘንድ አይችሉም። ነገር ግን ይህን እመሰክርልሃለሁ፤ በሕጉ ያለውን በነቢያትም የተጻፉትን ሁሉ አምኜ የአባቶቼን አምላክ እነርሱ ኑፋቄ ብለው እንደሚጠሩት መንገድ አመልካለሁ፤ እነዚህም ራሳቸው ደግሞ የሚጠብቁት ጻድቃንም ዓመፀኞችም ከሙታን ይነሱ ዘንድ እንዳላቸው ተስፋ በእግዚአብሔር ዘንድ አለኝ። ስለዚህ እኔ ደግሞ በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ሁልጊዜ ነውር የሌለባት ሕሊና ትኖረኝ ዘንድ እተጋለሁ። ከብዙ ዓመትም በኋላ ለሕዝቤ ምጽዋትና መሥዋዕት አደርግ ዘንድ መጣሁ፤ ይህንም ሳደርግ ሳለሁ ሕዝብ ሳይሰበሰብ ሁከትም ሳይሆን በመቅደስ ስነጻ አገኙኝ። ነገር ግን በእኔ ላይ ነገር ያላቸው እንደሆነ በፊትህ መጥተው ይከሱኝ ዘንድ የሚገባቸው ከእስያ የመጡ አንዳንድ አይሁድ አሉ። ወይም በመካከላቸው ቆሜ ዛሬ ስለሙታን መነሳት በፊታችሁ በእኔ ይፈረዱብኛል ብዬ ከጮኽሁት ከዚህ ከአንድ ነገር በቀር በሸንጎ ፊት ቆሜ ሳለሁ ከእኔ አንድ ዓመጻ ያገኙ እንደሆነ እነዚህ ራሳቸው ይናገሩ።
ፊልክስ ግን የመንገዱን ነገር አጥብቆ አውቆአልና የሻለቃው ሉስዮስ በወረደ ጊዜ ነገራችሁን እቆርጣለሁ ብሎ ወደፊት አዘገያቸው።»
መዝ 49:3

- እግዚአብሔርሰ ገሀደ ይመጽእ
  ወአምላክነ ኢያረምም
  እሳት ይነድድ ቅድሜሁ።

- እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል።
  አምላካችን ይመጣል ዝምም አይልም።
  እሳት በፊቱ ይቃጠላል።

ማቴ 24፥1-36 «ኢየሱስም ከመቅደስ ወጥቶ ሄደ። ደቀመዛሙርቱም የመቅደሱን ግንቦች ሊያሳዩት ቀረቡ። እርሱ ግን መልሶ ይህን ሁሉ ታያላችሁን? እውነት እላችኋለሁ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ አይቀርም አላቸው። እርሱም በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ ደቀመዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው ንገረን ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው? አሉት። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፡ ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ። ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ። ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፤ ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠበቁ አትደንግጡ። ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው። ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሳልና፤ ራብም ቸነፍርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ሥፍራ ይሆናል፤ እነዚህም ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው።
በዚያን ጊዜ ለመከራ አሳልፈው ይሰጡአችኋል፣ ይገድሉአችሁማል፣ ስለ ስሜም በአሕዛብ ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ። በዚያን ጊዜም ብዙዎች ይሰናከላሉ፤ እርስ በእርሳቸውም አሳልፈው ይሰጣጣሉ፤ እርስ በእርሳቸውም ይጣላሉ፤ ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትም ይነሳሉ ብዙዎችንም ያስታሉ፤ ከዓመፃም ብዛት የተነሳ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች። እስከመጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል። ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል። በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል።

እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰችው ሥፍራ ቆሞ ስታዩ አንባቢው ያስተውል። በዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉት ወደ ተራራዎች ይሽሹ፤ በሠገነትም ያለ በቤቱ ያለውን ሊወስድ አይውረድ። በእርሻም ያለ ልብሱን ይወስድ ዘንድ ወደኋላው አይመለስ። በዚያችም ወራት ለእርጉዞችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው። ነገር ግን ሽሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ። በዚያን ግዜ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያልሆነ እንግዲህም ከቶ የማይሆን ታለቅ መከራ ይሆናልና። እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር። ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ። በዚያን ጊዜ ማንም እነሆ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ፤ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሳሉና ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ። እነሆ አስቀድሜ ነገርኋችሁ። እንግዲህ እነሆ በበረሀ ነው ቢሉአችሁ አትውጡ፤ እነሆ በእልፍኝ ነው ቢሉአችሁ አትመኑ። መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና፤ በድን ወዳለበት በዚያ አሞራዎች ይሰበሰባሉ።
ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል፤ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፤ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፤ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ። በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፤ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ። የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል፤ መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፤ ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ።
ምሳሌውንም ከበለስ ተማሩ፤ ጫፍዋ ሲለሰልስ ቅጠልዋም ሲያቆጠቁጥ ያን ጊዜ በጋ እንደቀረበ ታውቃላችሁ። እንዲሁ እናንተ ደግሞ ይህን ሁሉ ስታዩ በደጅ እንደቀረበ እወቁ። እውነት እላችኋለሁ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም። ሰማይና ምድር ያልፋል ቃሌ ግን አያልፍም።
ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም።»
ቅዳሴ - ዘአትናቴዎስ

---

## 6. ገብርሄር

ስድስተኛው ሰንበትና ሳምንቱ ገብርኄር የተባለበት ምክንያት በዚሁ ሰንበት የሚዘመረው ጾመ ድጓ ከዋዜማው ጀምሮ «ገብር ኄር ወገብር ምእመን ገብር ዘአሥመሮ ለእግዚኡ። ጌታውን ያስደሰተው አገልጋይ ታማኝና ቸር አገልጋይ ነው። ገብር ኄር ወገብር ምእመን ዘበውኁድ ምእመነ ኮነከ ዲበ ብዙኀ እሰይመከ። በጥቂቱ የታመንህ ቸር አገልጋይ ሆይ በብዙ እሾምሃለሁ» ዘበምልክናከ ሠናየ ገብርከ ብፁዕ አንተ ገብር ኄር። በሹመትህ በጎ የሠራህ ምእመን ዘይረክቦ እግዚኡ በምግባረ ሠናይ ወይሰይሞ ዲበኩሉ ንዋዩ በደግ ሥራ ጌታው የሚያገኘውና በገንዘቡ ሁሉ ላይ የሚሾመው ቸርና የታመነ አገልጋይ ማነው? «ለአግብርት ግዕዛን ለማሃይምናን ሰላም ዛቲ ዕለት ሰንበተ ክርስቲያን ይቺ ዕለት የክርስቲያን ሰንበት ለአገልጋዮች ነፃነት ለአማኞች ሰላም ናት። ኩኑ እንከ ከመ አግብርት ኄራን ወከመ አግብርተ ክርስቶስ ምእመናን እለ ይጸንሑ እግዚኦሙ እስከ የአቱ እምከብካብ ዘበሰማያት፡- እንግዲህ እንደ ቸሮች አገልጋዮችና በሰማይ ባለው መንግሥት እግዚአብሔር እስከሚገቡ ድረስ ጌታቸውን ደጅ እንደሚጠኑ እንደ ክርስቶስ አገልጋዮች ሆኑ። ጹሙ ወጸልዩ ከመ አግብርት ተቀነዩ፡- ጹሙ ጸልዩ እንደ በጎ አገልጋዮች ለእግዚአብሔር ተገዙ እያለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የካህናትና የምእመናንን የጽድቅ ሥራ በመልካም አገልጋይ ሥራ የኃጥአንን የበደል ሥራ በክፉ አገልጋይ ሥራ እያመሳሰለ በወንጌል ያስተማረውን ትምህርት በአጠቃላይ ስለጻድቃንና ኃጥአን በምሳሌ የተናገረውን ቃለ ወንጌል እየጠቃቀሰና እያነሣሣ ስለሚዘመር ሰንበቱ ገብር ኄር ተብሎ ተጠርቷል።
ስለዚህ ይህ ሰንበት የጻድቃን መታሰቢያ ዕለት ነው። በዚህ ዕለተ ሰንበት መታሰቢያነት የተሰጠውን የገብር ኄርን የምሳሌ ትምህርት የምናገኘው ቀጥሎ በተጠቀሱት የወንጌል ክፍሎች ነው። /ማቴ 25:14-46፤ ሉቃ 19:12-27፤ ማቴ 13:12/።
ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ምዕራፎችና ቁጥሮች ብንመለከት ስለ ገብርኄር ምሳሌነትና ስለ ጻድቃን ዋጋ እንዲሁም ስለ ኃጥአን ፍዳ የተጻፉትን የምሳሌ አነጋገሮች ለማግኘት እንችላለን።
2ጢሞ.2:1-16 «እንግዲህ ልጄ ሆይ አንተ በክርስቶስ እየሱስ ባለው ጸጋ በርታ ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ። እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ አብረኸኝ መከራ ተቀበል። የሚዘምተው ሁሉ ለጦር ያስከተተውን ደስ ያሰኝ ዘንድ ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን አያጠላልፍም። ደግሞም በጨዋታ የሚታገል ማንም ቢሆን እንደሚገባ አድርጎ ባይታገል የድሉን አክሊል አያገኝም። የሚደክም ገበሬ ፍሬውን ከሚበሉት መጀመሪያ እንዲሆን ይገባዋል የሚለውን ተመልከት ጌታም በነገር ሁሉ ማስተዋልን ይሰጥህ።
በወንጌል እንደምሰብከው ከሙታን የተነሣውን ከዳዊት ዘርም የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶን አስብ። ይህንም በመስበክ እንደ ክፉ አድራጊ እስክታሠር ድርስ መከራ እቀበላለሁ። የእግዚአብሔር ቃል ግን አይታሠርም። ስለዚህ እነርሱ ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን መዳን ከዘላለም ክብር ጋር እንዲያገኙ ስለተመረጡ በነገር ሁሉ እጸናለሁ። ቃሉ የታመነ ነው። እንዲህ የሚለው ከእርሱ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት

እንኖራለን፤ ብንጸና ከእርሱ ጋር ደግሞ እንነግሣለን፤ ብንክደው እርሱ ደግሞ ይክደናል፤ ባናምነው እርሱ የታመነ ሆኖ ይኖራል፤ ራሱን ሊክድ አይችልምና።
ይህን አሳስባቸው፤ በቃልም እንዳይጣሉ በእግዚአብሔር ፊት ምከራቸው። ይህ ምንም የማይረባ የሚሰሙትንም የሚያፈርስ ነውና። የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ፤ ነገር ግን ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍ ራቅ።»

1ጴጥ5፥1-12 «እንግዲህ እኔ ከእነርሱ ጋር ሽማግሌ የክርስቶስም መከራ ምስክር ደግሞም ሊገለጥ ካለው ክብር ተካፋይ የሆንሁ በመካከላቸው ያሉትን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ፤ በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጐብኙት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ። የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ። እንዲሁም ጐበዞች ሆይ ለሽማግሌዎች ተገዙ፤ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደልብስ ታጠቁ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል።
እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ፤ እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት። በመጠን ኑሩ ንቁም ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤ በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት። በክርስቶስ ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል፣ ያጸናችሁማል፣ ያበረታችሁማል። ለእርሱ ክብርና ኃይል እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን አሜን።»
የሐዋ.ሥራ 1፥6-9 «ቴዎፍሎስ ሆይ ኢየሱስ የመረጣቸውን ሐዋርያትን በመንፈስ ቅዱስ ካዘዛቸው በኋላ እስከ ዐረገበት ቀን ድረስ ያደርገውና ያስተምረው ዘንድ ስለጀመረው ሁሉ መጀመሪያውን ነገር ጻፍሁ፤ ደግሞ አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔርም መንግሥት ነገር እየነገራቸው በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው። ከእነርሱም ጋር አብሮ ሳለ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አዘዛቸው። ነገር ግን ከእኔ የሰማችሁትን አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቁ፤ ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ አለ። እነርሱም በተሰበሰቡ ጊዜ ጌታ ሆይ በዚህ ወራት ለእሥራኤል መንግሥትን ትመልሳለህን? ብለው ጠየቁት ። እርሱም፦ አብ በገዛ ሥልጣኑ ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ ለእናንተ አልተሰጣችሁም። በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ። ይህንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው።»
መዝ 39፡8

- ከመ እንግር ፈቃደከ መከርኩ አምላኪየ
  ወሕግከኒ በማዕከለ ከርሥየ
  ዜኖኩ ጽድቀከ በማኅበር ዐቢይ።

- አምላኪየ ሆይ ፈቃድህን ለማድረግ ወደድሁ
  ሕግህም በልቤ ውስጥ ነው።
  በታላቅ ጉባኤ ጽድቅህን አወራሁ።

ማቴ 25፥14-31 «ወደ ሌላ አገር የሚሄድ ሰው ባሮቹን ጠርቶ ያለውን ገንዘብ እንደሰጣቸው እንዲሁ ይሆናል፤ ለእያንዳንዱ እንደ ዓቅሙ ለአንዱ አምስት መክሊት ለአንዱ ሁለት ለአንዱም አንድ ሰጠና ወደ ሌላ አገር ወዲያው ሄደ። አምስት መክሊትም የተቀበለው ሄዶ ነገደበት ሌላም አምስት አተረፈ፤ እንዲሁም ሁለት የተቀበለው ሌላ ሁለት አተረፈ። አንድ የተቀበለው ግን ሄዶ ምድርን ቈፈረና የጌታውን ገንዘብ ቀበረ። ከብዙ ዘመንም በኋላ የእነዚያ ባሮች ጌታ መጣና ተቈጣጠራቸው። አምስት መክሊት የተቀበለውም ቀረበና ሌላ አምስት መክሊት አስረክቦ ጌታ ሆይ አምስት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር፤ እነሆ ሌላ አምስት መክሊት አተረፍሁበት አለ። ጌታውም መልካም አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ፤ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለሁ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው። ሁለት መክሊትም የተቀበለው ደግሞ ቀርቦ ጌታ ሆይ ሁለት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር፤ እነሆ ሌላ ሁለት መክሊት አተርፍሁበት አለ። ጌታውም መልካም አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ፤ በጥቂቱ ታምነሃል በብዙ እሾምሃለህ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው። አንድ መክሊትም የተቀበለው ደግሞ ቀርቦ ጌታ ሆይ ካልዘራህባት የምታጭድ ካልበተንህባትም የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን አውቃለሁ። ፈራሁም ሄጄም መክሊትህን በምድር ቀበርሁት፤ እነሆ መክሊትህ አለ አለ። ጌታውም መልሶ እንዲህ አለው፦ አንተ ክፉና ሃኬተኛ ባሪያ ካልዘራሁባት እንዳጭድ ካልበተንሁባትም እንድሰበስብ ታውቃለህን? ስለዚህ ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሰጠው በተገባህ ነበር። እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር። ስለዚህ መክሊቱን ውሰዱበት አሥር መክሊትም ላለው ስጡት ላለው ሁሉ ይሰጠዋልና ይበዛለትማል፤ ከሌለው ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል። የማይጠቅመውንም ባሪያ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል። የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል።
ቅዳሴ - ዘባስልዮስ

## 7. ኒቆዲሞስ

ሰባተኛው ሰንበትና ሳምንቱ ኒቆዲሞስ የተባለበት ምክንያት በዚሁ ሰንበት የሚዘመረው ጾመ ድጓ ከዋዜማው ጀምሮ «ወሀሎ አሐዱ ብእሲ እምፈሪሳውያን ዘስሙ ኒቆዲሞስ መልአከሙ ለአይሁድ ዞሖረ ኀቤሁ ቀዲሙ ሌሊተ ወይቤሎ ለኢየሱስ ዕጓለ አንበሳ ሰከብከ ወኖምከ አንሥአኒ በትንሣኤከ፡- ስሙ ኒቆዲሞስ የሚባል የአይሁድ አለቃ የሆነ ከፈሪሳውያን ወገን አንድ ሰው ነበረ። እሱ አስቀድሞ ሌሊት ሄዶ ኢየሱስን በመቃብር አንቀላፋህ በትንሣኤህ አንሣኝ» ያለው ነው። ኒቆዲሞስ ሰገደ መንፈቀ ሌሊት ለዘቀደሳ ለሰንበት፡- ሰንበትን ለአከበራት ጌታ ኒቆዲሞስ ኢየሱስን ረቢ አብ መምህር ሆንህ ከአብ ዘንድ እንደመጣህ እናምንብሃለን አለው።» እያለ ኒቆዲሞስ ሌሊት ወደ ጌታችን ኢየሱስ እየሔደ ይሰግድ እንደነበረና ምሥጢረ ጥምቀትን ከእሱ እንደተማረ እየጠቃቀሰ እያነሣሣ ስለሚዘምር ይህ ሰንበት ለዚሁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኒቆዲሞስ ከጌታ ለመማሩ መታሰቢያ ሆኖ ስለተሰጠ ነው፡ የዚህ በዓል ታሪክ ዝርዝር ሁኔታው በዮሐንስ ወንጌል ምዕ 3 ቁጥ 1 እስከ 21 ተጽፏል።

በዚህ ክፍለ ወንጌል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኒቆዲሞስ ምሥጢረ ጥምቀትን ብቻ ሳይሆን ርደቱን፣ ስቅለቱን፣ አዳኝነቱን አስተምሮታል። ኒቆዲሞስ ከአርማትያሱ ከዮሴፍ ጋር ሆኖ ጌታን የገነዘው ታላቅ ሰው ነው። ስለዚህ ይህ ሰንበት ከዚህ ጀምሮ የኒቆዲሞስ መታሰቢያ እስከ 3 ቀን ይከበራል ማለት ማክሰኞ ድረስ የኒቆዲሞስ ቀኖች ናቸው።

ሮሜ 7፡1-19 «ወንድሞች ሆይ ሕግን ለሚያውቁ እናገራለሁና ሰው ባለበት ዘመን ሁሉ ሕግ እንዲገዛው አታውቁምን? ያገባች ሴት ባልዋ በሕይወት ሲኖር ከእርሱ ጋር በሕግ ታስራለችና፤ ባልዋ ቢሞት ግን ስለ ባል ከሆነው ሕግ ተፈትታለች። ስለዚህ ባልዋ በሕይወት ሳለ ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ ትባላለች፤ ባልዋ ቢሞት ግን ከሕጉ አርነት ወጥታለችና ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ አይደለችም።

እንዲሁ ወንድሞቼ ሆይ እናንተ ደግሞ በክርስቶስ ሥጋ ለሕግ ተገድላችኋል ለእግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ እናንተ ለሌላው ከሙታን ለተነሣው ለእርሱ ትሆኑ ዘንድ። በሥጋ ሳለን በሕግ የሚሆን የኃጢአት መሻት ለሞት ፍሬ ሊያፈራ በብልቶቻችን ይሠራ ነበርና፤ አሁን ግን ለእርሱ ለታሰርንበት ስለ ሞትን ከሕግ ተፈትተናል ስለዚህም በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ እንገዛለን እንጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ አይደለም።

እንግዲህ ምን እንላለን? ሕግ ኃጢአት ነውን? አይደለም፤ ነገር ግን በሕግ ባይሆን ኃጢአትን ባላወቅሁም ነበር፤ ሕጉ አትመኝ ባላለ ምኞትን ባላወቅሁም ነበርና። ኃጢአት ግን ምክንያት አግኝቶ ምኞትን ሁሉ በትእዛዝ ሠራብኝ፤ ኃጢአት ያለ ሕግ ምውት ነውና። እኔም ዱሮ ያለሕግ ሕያው ነበርሁ፤ ትእዛዝ በመጣች ጊዜ ግን ኃጢአት ሕያው ሆነ እኔም ሞትሁ፤ ለሕይወትም የተሰጠችውን ትእዛዝ እርስዋን ለሞት ሆና አገኘኋት፤ ኃጢአት ምክንያት አግኝቶ በትእዛዝ አታሎኛልና በእርስዋም ገድሎኛል። ስለዚህ ሕጉ ቅዱስ ነው ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት።

እንግዲህ በጎ የሆነው ነገር ለእኔ ሞት ሆነብኝን? አይደለም ነገር ግን ኃጢአት ሆነ፤ ኃጢአትም በትእዛዝ ምክንያት ያለልክ ኃጢአተኛ ይሆን ዘንድ ኃጢአትም እንዲሆን ይገለጥ ዘንድ በጎ በሆነው ነገር ለእኔ ሞትን ይሠራ ነበር። ሕግ መንፈሳዊ እንደሆነ እናውቃለንና፤ እኔ ግን ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ። የማደርገውን አላውቅምና፤ የምጠላውን ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም በእኔ የሚያድር ኃጢአት ነው። እንጂ። በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና፤ ፈቃድ አለኝና መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም የማልወደውን ክፉውን ነገር አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም።»

1 ዮሐ 4፡18 « ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም ፍርሃት ቅጣት አለውና፤ የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም። እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን። ማንም እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል? እግዚአብሔርንም የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችን።»

የሐዋ.ሥራ 5፡34-42 «ነገር ግን በሕዝቡ ሁሉ ዘንድ የከበረ የሕግ መምህር ገማልያል የሚሉት አንድ ፈሪሳዊ በሸንጎ ተነሥቶ ሐዋርያትን ጥቂት ፈቀቅ እንዲያደርጉአቸው አዘዘ። እንዲህም አላቸው የእሥራኤል ሰዎች ሆይ ስለ እነዚህ ሰዎች ምን እንደምታደርጉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ከዚህ ወራት አስቀድሞ ቴዎዳስ እኔ ታላቅ ነኝ ብሎ ተነሥቶ ነበርና አራት መቶ የሚያህሉ ሰዎችም ከእርሱ ጋር ተባበሩ፤ እርሱም ጠፋ የሰሙትም ሁሉ ተበተኑ እንደ ምናምንም ሆኑ። ከዚህ በኋላ ሰዎች በተጻፉበት ዘመን የገሊላው ይሁዳ ተነሣ ብዙ ሰዎችንም አሸፍቶ አስከተለ፤ ከእግዚአብሔር እንደሆነ ግን ታጠፉአቸው ዘንድ አይቻላችሁም፤ በእርግጥ ከእግዚአብሔር ጋር ስትጣሉ ምናልባት እንዳትገኙ።

ሰሙትም ሐዋርያትንም ወደ እነርሱ ጠርተው ገረፉአቸው፤ በኢየሱስም ስም እንዳይናገሩ አዝዘው ፈቱአቸው። እነርሱም ስለስሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለ ተቈጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ፤ ዕለት ዕለትም በመቅደስና በቤታቸው ስለ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ማስተማርንና መስበክን አይተውም ነበር። »

መዝ 16፡3

- ሐወጽከኒ ሌሊተ ወፈተንኮ ለልብየ
  አመከርከኒ ወኢተረክበ ዓመጻ በላዕሌየ
  ከመ ኢይንብብ አፉየ ግብረ እጓለ እመሕያው

- ልቤን ፈተንኸው በሌሊትም ጐበኘኸኝ::
  ፈተንኸኝ ምንም አላገኘህብኝም::
  የሰውን ሥራ አፌ እንዳይናገር ፈቃዴ ነው::

ዮሐ 3:1-12 «ከፈሪሳውያንም ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ፤ እርሱም በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ መምህር ሆይ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለምና መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን አለው:: ኢየሱስም መልሶ እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው:: ኒቆዲሞስም፡- ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንደ ይችላልን? አለው:: ኢየሱስም መለሰ እንዲህ ሲል፡- እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም:: ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው:: ዳግመኛ ልትወለዱ ያስፈልጋችኋል ስላልሁህ አታድንቅ:: ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል ድምፁንም ትሰማለህ ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው:: ኒቆዲሞስም መልሶ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? አለው:: ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፡- አንተ የእሥራኤል መምህር ስትሆን ይህን አታውቅምን? እውነት እውነት እልሃለሁ የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውንም እንመሰክራለን ምስክራችንንም አትቀበሉትም:: ስለምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ ካላመናችሁ ስለሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ?»
ቅዳሴ - ዘእግዝእትነ /ጐሥዓ/

---

## 8. ሆሣዕና

ስምንተኛው ሰንበት በኋላው ካለው ከረቡዕ ጀምሮ ሆሣዕና በመባል ይታወቃል:: ይህን ስም ያገኘበት ምክንያት በዚህ ሰንበትና በዋዜማዎቹ ዕለታት የሚዘመረው ጾመ ድጓ «ሆሣዕና በአርያም የሆሣዕናን ቃል በእየቦታው እየጠቀሰና እያነሣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እየተመሰገነና እየተዘመረለት በአህያ ውርንጭላ ተቀምጦ ኢየሩሳሌም የገባበትን ሁኔታ እየተረከ ስለሚዘምር ይህ ሰንበት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጌትነትና በክብር በውዳሴና ቅዳሴ ሆሣዕና በአርያም እየተባለ በሽማግሌዎችና በሕፃናት አንደበት በድንጋዮች ልሳን ሳይቀር እየተመሰገነ ኢየሩሳሌም በአህያ ተቀምጦ ለመግባቱ መታሰቢያ ሆኖ ስለተሰጠ ነው:: የዚህ በዓል ዝርዝር ሁኔታው ቀጥሎ ባሉት ምዕራፎችና ቁጥሮች ተዘርዝሮ ይገኛል:: /ማቴ 21:1-17፣ ማር 11:1-10፣ ሉቃ 19:29-38፣ ዮሐ 12:12-15፣ ዘካ 9:9፣ 2ነገ 9:13፣ መዝ 117:25-26፣ ኢሳ 56:7፣ ኤር 7:12፣ መዝ 8:2/



ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ምዕራፎችና ቁጥሮች በጽሞና ብንመለከት ስለሆሣዕና በትንቢት የተነገሩትንና በድርጊት የተፈጸሙትን መረዳት ይቻላል::
ከዚህ በላይ እንደተጠቀሰው የሰንበታቱ ስያሜ በቂ የሆነ የቅዱሳት መጻሕፍት ታሪክ ድጋፍ ያለውና የጾመ ድጓውን ባሕል የተከተለ መሆኑን መገንዘብ ይገባል::

ዕብ 8:1-13 «ከተናገርነውም ዋና ነገሩ ይህ ነው:: በሰማያት በግርማው ዙፋን ቀኝ የተቀመጠ እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት አለን:: እርሱም የመቅደስና የእውነተኛይቱ ድንኳን አገልጋይ ነው:: እርሱዋም በሰው ሳይሆን በጌታ የተተከለች ናት:: ሊቀ ካህናት ሁሉ መባንና መሥዋዕትን ሊያቀርብ ይሾማልና፤ ስለዚህም ለዚህ ደግሞ የሚያቀርበው አንዳች ሊኖረው የግድ ነው:: እንግዲህ በምድር ቢኖርስ እንደ ሕግ መባን የሚያቀርቡት ስላሉ ካህን እንኳ ባልሆነም እነርሱም ሙሴ ድንኳኒቱን ሊያደርግ ሳለው እንደ ተረዳ ለሰማያዊ ነገር ምሳሌና ጥላ የሚሆነውን ያገለግላሉ:: በተራራው እንደ ተገለጠልህ ምሳሌ ሁሉን ታደርግ ዘንድ ተጠንቀቅ ብሎት ነበርና አሁን ግን ለሚሻል ተስፋ ቃል በተመሠረተ በሚሻል ኪዳን ደግሞ መካከለኛ እንደሚሆን ለዚያ ልክ እጅግ የሚሻል አገልግሎት አግኝቶአል:: ፊተኛው ኪዳን ነቀፋ ባይኖረው ለሁለተኛው ስፍራ ባልተፈለገም ነበር::
እነርሱን እየነቀፈ ይላቸዋልና፡- እነሆ ከእሥራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል ይላል ጌታ ከግብፅ አገር አወጣቸው ዘንድ እጃቸውን በያዝሁበት ቀን ከአባቶቻቸው ጋር እንደገባሁት ኪዳን አይደለም እነርሱ በኪዳኔ አልጸኑምና እኔም ቸል አልኋቸው ይላል ጌታ ከዚያ ወራት በኋላ ከእሥራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነውና ይላል ጌታ ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ በልባቸውም እጽፈዋለሁ እኔም አምላክ እሆንላቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑልኛል:: እያንዳንዱም ጐረቤቱን እያንዳንዱም ወንድሙን ጌታን እወቅ ብሎ አያስተምርም ከታናሹ ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉ

ያውቁኛልና ዓመፃቸውን እምራቸዋለሁና ኃጢአታቸውንም ደግሜ አላስብም። አዲስ በማለቱ ፊተኛውን አስረጅቶአል አሮጌና ውራጅ የሆነውስ ሊጠፋ ቀርቦአል።»

1ጴጥ1፡13-25 «ስለዚህ የልቡናችሁን ወገብ ታጥቃችሁና በመጠን ኖራችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ የምታገኙትን ጸጋ ፈጽማችሁ ተስፋ አድርጉ እንደሚታዘዙ ልጆች ባለማወቃችሁ አስቀድሞ የኖራችሁበትን ምኞት አትከተሉ። ጻሩ ግን እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ። ለሰው ፊትም ሳያዳላ በእያንዳንዱ ላይ እንደሥራው የሚፈርደውን አባት ብላችሁ ብትጠሩ በእንግድነታችሁ ዘመን በፍርሃት ኑሩ። ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደተዋጃችሁ ታውቃላችሁ ዓለም ሳይፈጠር እንኳ አስቀድሞ ታወቀ። ነገር ግን እምነታችሁና ተስፋችሁ በእግዚአብሔር ይሆን ዘንድ ከሙታን ላስነሣው ክብርንም በሰጠው በእግዚአብሔር በእርሱ ስለምታምኑ ስለ እናንተ በዘመኑ መጨረሻ ተገለጠ።
ለእውነት እየታዘዛችሁ ግብዝነት ለሌለበት በወንድማማች መዋደድ ነፍሳችሁን አንጽታችሁ እርስ በርሳችሁ ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ። ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ፤ ሥጋ ሁሉ እንደ ሣር ክብሩም ሁሉ እንደ ሣር አበባ ነውና ሣሩ ይጠወልጋል አበባውም ይረግፋል የጌታ ቃል ግን ለዘላለም ይኖራል፤ በወንጌልም የተሰበከላችሁ ቃል ይህ ነው።»

የሐዋ.ሥራ 8፡26-40 «የጌታም መልአክ ፊልጶስን ተነሥተህ በደቡብ በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው ምድረ በዳ ወደ ሆነ መንገድ ሂድ አለው። ተነሥቶም ሄደ። እነሆም ህንዳኬ የተባለች የኢትዮጲያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ በገንዘብዋም ሁሉ የሠለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር፤ ሲመለስም በሰረገላ ተቀምጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር። መንፈስም ፊልጶስን፡- ወደዚህ ሰረገላ ቅረብና ተገናኝ አለው። ፊልጶስም ሮጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ሲያነብ ሰማና፡- በእውኑ የምታነበውን ታስተውለዋለህን? አለው። እርሱም፡- የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል? አለው። ወጥቶም ከእርሱ ጋር ይቀመጥ ዘንድ ፊልጶስን ለመነው። ያነበውም የነበረ የመጽሐፍ ክፍል ይህ ነበረ፤
እንደበግ ወደ መታረድ ተነዳ፤ የበግ ጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል እንደሁ አፋን አልከፈተም
በውርደቱ ፍርዱ ተወገደ፤ ሕይወቱ ከምድር ተወግዳለችና ትውልዱንስ ማን ይናገራል?
ጃንደረባውም ለፊልጶስ መልሶ፡- እባክህ ነቢዩ ይህ ስለማን ይናገራል? ስለራሱ ነውን ወይስ ስለሌላ? አለው።
ፊልጶስም አፋን ከፈተ ከዚህም መጽሐፍ ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት። በመንገድም ሲሄዱ ወደ ውኃ ደረሱ። ጃንደረባውም እነሆ ውኃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድን ነው? አለው። ፊልጶስም፡- በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶአል አለው። መልሶም ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ አለ። ሰረገላውም ይቆም ዘንድ አዘዘ፤ ፊልጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውኃ ወረዱ አጠመቀውም። ከውኃውም ከወጡ በኋላ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ነጠቀው፤ ጃንደረባውም ሁለተኛ አላየውም ደስ ብሎት መንገዱን ይሄድ ነበርና። ፊልጶስ ግን በአዛጦን ተገኘ ወደ ቂሣርያም እስኪመጣ ድረስ እየዞረ በከተማዎች ሁሉ ወንጌልን ይሰብክ ነበር።

መዝ 80፡3

- ንፍሑ ቀርነ በዕለተ ሠርቅ
  በዕምርት ዕለት በዓልነ
  እስመ ሥርዓቱ ለእስራኤል ውእቱ።

- በመባቻ ቀን በከፍተኛው በዓላችን ቀን
  መለከትን ንፉ
  ለእሥራኤል ሥርዓቱ ነውና ።

ዮሐ 12፡1-12 «ከፋሲካም በፊት በስድስተኛው ቀን ኢየሱስ ከሙታን ያስነሣው አልዓዛር ወደ ነበረበት ወደ ቢታንያ መጣ። በዚያም እራት አደረጉለት። ማርታም ታገለግል ነበር። አልዓዛር ግን ከእርሱ ጋር ከተቀመጡ-ት አንዱ ነበረ። ማርያምም ዋጋው እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶስ ሽቱ ንጥር ወስዳ የኢየሱስን እግር ቀባች፤ በጠጉርዋም እግሩን አበሰች፤ ቤቱም ከናርዶስ ሽቱ ሞላ። ነገር ግን ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ ሊሰጠው ያለው የስምዖን ልጅ የአስቆሮቱ ይሁዳ፡- ይህ ሽቱ በሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለምን ነው? አለ። ይህንም የተናገረ ሌባ ስለነበረ ነው እንጂ ለድሆች ተገድዶላቸው አይደለም፤ ከረጢትም ይዞ በውስጡ ከሚገባው ይወስድ ስለነበረ ነው። ኢየሱስም፡- ለምቀበርበት ቀን እንድትጠብቀው ተውአት፤ ድሆችስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም አለ።

ከአይሁድም ብዙ ሕዝብ በዚያ እንደ ነበረ አውቀው መጡ፣ ከሙታንም ያስነሣውን አልዓዛርን ደግሞ እንዲያዩ ነበረ እንጂ ስለ ኢየሱስ ብቻ አይደለም። የካህናት አለቆችም አልዓዛርን ደግሞ ሊገድሉት ተማከሩ። ከአይሁድ ብዞዎች ከእርሱ የተነሣ ሄደው በኢየሱስ ያምኑ ነበርና። »
መዝ 117:26

- ቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር
  ባረክናክሙ እምቤተ እግዚአብሔር
  እግዚአብሔር እግዚእ አስተርአየ ለነ።

- በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው።
  ከእግዚአብሔር ቤት መረቅናችሁ።
  እግዚአብሔር አምላክ ነው ለእኛም በራልን።

ሉቃ.19:1-11 «ወደ ኢያሪኮም ገብቶ ያልፍ ነበር። እነሆም ዘኬዎስ የሚባል ሰው እርሱም የቀራጮች አለቃ ነበረ ባለጠጋም ነበረ። ኢየሱስንም የትኛው እንደ ሆነ ሊያይ ይፈልግ ነበር፤ ቁመቱም አጭር ነበረና ስለ ሕዝቡ ብዛት አቃተው። በዚያችም መንገድ ያልፍ ዘንድ አለውና ያየው ዘንድ ወደ ፊት ሮጦ በአንድ ሾላ ላይ ወጣ። ኢየሱስም ወደዚያ ስፍራ በደረሰ ጊዜ አሻቅቦ አየና፦ ዘኬዎስ ሆይ ዛሬ በቤትህ እውል ዘንድ ይገባኛልና ፈጥነህ ውረድ አለው። ፈጥኖም ወረደ በደስታም ተቀበለው። ሁሉም አይተው፦ ከኃጢአተኛ ሰው ጋር ሊውል ገባ ብለው አንጐራጐሩ። ካለኝ ሁሉ እኩሌታውን ለድሆች እሰጣለሁ ማንንም በሐሰት ከስሼ እንደ ሆንሁ አራት እጥፍ እመልሳለሁ አለው። ኢየሱስም፦ እርሱ ደግሞ የአብርሃም ልጅ ነውና ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆኖለታል የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና አለው።»
ቅዳሴ - ዘጎርጎርዮስ

# ወስብሐት ለእግዚአብሔር